# ግም ፣ገማ

ባራቱም ማዕዘን ፣ ጨልሞ ፣ ባገር ላይ
ቆራጥ ፣ ባገር ጠፍቶ ፣ ሰው ሆኖ ፣ ወላዋይ
ህሊናውን ሽጦ ፣ ምሁር ፣ ሆኖ አድርባይ
ጠ/ሚኒስትሩም ፣ ቀጣፊ ፣ ቃል አባይ
ሁሉን ሲሸመጥጥ ፣ ወጥቶ ባደባባይ
ጋዜጠኛም ሁሉ ፣ ለመጣው አውደልዳይ
ተስፋ ፣ በሃገር ጠፍቶ ፣ እርቆ እንደሰማይ
የኢትዮጵያ ትንሳዔ ፣ ጨልሟል አይታይ ።

አላበቃ ብሎ ፣ የኢትዮጵያ ፈተና
የጠገበው ሄዶ ፣ አዲስ ጅብ ፣ መጣና
በልቶ የማይጠረቃ ፣ ቢዝቀው በቁና
ያየውን የሚመኝ ፣ ህልሙ የምርቃና
ለኢትዮጵያ መፍረስ ፣ ለሃገር ብተና
ሲራወጥ ያመሻል ፣ ሰው ፣ ባገር ጠፋና
ከጠላት በባሰ ፣ ይላል ፣ ደፋ ቀና ።

የተማረ ደነዝ ፣ ፊደል እንኳን ፣ ቆጥሮ
ወንድሙን ሊያጠፋ ፣ በዘውጌነት ሰክሮ
ኬኛ ፣ ኬኛ ፣ የሚለው ፣ በታመመ ዐይምሮ
እራሱን አስውቦ ፣ ሌላውን አጥቁሮ
የተቅበዘበዘው ፣ ቄሮ ያሉት ፣ ቀርቀሮ
ገጀራውን ታጥቆ ፣ የወጣው ፎክሮ
የሚያነደው እሳት ፣ ባጥፊዎች ተመክሮ
በጫራት ፣ እሳት ውስጥ ፣ ይገባታል ዞሮ ።

አገር የሚመራው ፣ ቁጭ ያለው ፣ ከማማ
የለበጣ ተረት ፣ ዲስኩር የሚያሰማ
እያፈናቀለ ፣ ንብረት የሚያስቀማ
ደሃ እያስለቀሰ ፣ ደሃን እያደማ
እንደ ፣ ደጋን ጎብጦ ፣ ያደገ ጠማማ
በነጋ በጠባ ፣ በኢ-ሐ-ደ-ግ ግምገማ
ሲረገጥ የኖረ ፣ ድንጋይ የማይሰማ
መደንፋቱን ትተህ ፣ እንዳበጠ ኮርማ
በድሉ ዋቅጅራን ፣ አስተውለህ ስማ
ዘመነ ወያኔ ፣ አይደለም ፣ ግም ፣ ገማ ።

ጆሮ ዳባ ማለት ፣ ሲኮን ባለተራ
ጊዜው የኛ ከሚል ፣ ከባዶ ፉከራ
ሰው ሁኑ ፣ እስቲ ዛሬ ፣ እንደሰው እናውራ
ግብዝ አትሁኑ ፣ አይንፋችሁ ጉራ
ካስተማረህ ጀግና ፣ በቅን እንድትሰራ
ትምህርትን ውሰዱ ፣ ከበድሉ ዋቅጅራ ።

ታዛቢው

April 3, 2019